የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፯
አዲስ አበባ ሚያዚያ ፩ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No. 47
ADDIS ABABA 9th, April 2019

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፳፫ /፪ሺ፲፩ ዓ.ም

የሕገ-መንግስትና የፌደራሊዝም አስተምህሮ ማዕከል ማቋቋሚያ አዋጅ……ገፅ ፲፩ሺ፩፻፺፬

## CONTENT

Proclamation No.1123 /2019

Constitutional and Federalism Indoctrination Center Establishment Proclamation...................page 11194

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፳፫/፪ሺ፲፩

**የሕገ-መንግስትና የፌደራሊዝም አስተምህሮ ማዕከልን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ**

የሕገ-መንግስትና ፌደራሊዝም አስተምህሮ ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን በየጊዜዉ እያጠና ክፍተቱን ለመሙላት የሚያስችል ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤

የሕገ-መንግሥትና ፌደራሊዝም አስተምህሮና ስርፀት ተደራሽነትን በማስፋት ሕገመንግሥታዊ ባህልን የተላበሰ ንቁና ሁለንተናዊ ተሳትፎ የሚያደርግ ማህበረሰብ መፍጠር በማስፈለጉ፤

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ ፶፭ (፩) በተሠጠው ሥልጣን መሠረት ይህን አዋጅ አውጥቷል:-

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የሕገ-መንግስትና ፌደራሊዝም አስተምህሮ ማዕከል ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፳፫ /፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## PROCLAMATION NO. 1123 /2019

**A PROCLAMATION TO ESTABLISH CONSTITUTIONAL AND FEDERALISM INDOCTRINATION CENTER**

**WHEREAS**, it has been found important to put in place a functional system to bridge the gap on Federalism and Constitutional Indoctrination through studies;

**WHEREAS**, it has become necessary to create active and disciplined society equipped with constitutional culture through expanding and promoting the doctrine of Constitution and Federalism;

**NOW, THERE FORE**, by the power given to the House of Peoples Representatives of Federal Democratic Republic of Ethiopia as per Article 55 (1) of the Constitution ,it is here by proclaimed as follows፡

### PART ONE

### GENERAL PROVISIONS

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Constitutional and Federalism Indoctrination Center Establishment Proclamation No. 1123/2019".

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ “የልህቀት ማእከላት” የሕገመንግሥትና በፌደራሊዝም አስተምህሮ ሂደቱን በሚያሳልጡት ላይ ከፍተኛ ሚና ያላቸው እንደ ትምህርት ተቋማት፣ የሚዲያና ስነጥበብ አካላት፣ የፐብሊክና የሲቪል ሰርቪስ ተቋማት፣ የፍትህና የጸጥታ አካላት እና የሙያና የብዙኃን ማህበራትን ያካትታል፤

፪/ “ባለድርሻ አካላት” ማለት በሕገ መንግስትና ፌደራሊዝም አስተምህሮ ረገድ ሚና ያላቸውን አካላት ያጠቃልላል፤

፫/ “ምክር ቤት” ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደሬሽን ምክር ቤት ነው፡፡

፬/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የማዕከሉ መቋቋም፣ ዓላማ፣ ስልጣንና ተግባር

**፫. መቋቋም**

፩/ የሕገ መንግስትና ፌደራሊዝም አስተምህሮ ማዕከል (ከዚህ በኋላ “ማዕከል” እየተባለ የሚጠራው) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪/ ማዕከሉ ለኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፌደሬሽን ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ “ምክር ቤት” እየተባለ ለሚጠራው) ተጠሪ ይሆናል፡፡

፫/ የማዕከሉ ዋና መስሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በክልሎች እና በከተማ አስተዳደሮች ቅርንጫፍ ሊከፍት ይችላል፡፡

**2. Definition**

In this Proclamation unless the context otherwise requires:-

1/ “Center of Excellence” includes Educational Institutions, Media and Art Center, Public and Civil Service Institutions, Justice and Security Organs, and Professional and Mass Based Associations that have significant role to facilitate the indoctrination process of the Constitution and Federalism;

2/ “Stakeholders” include Organs having role in Indoctrination of Constitution and Federalism in their duties;

3/ “House” mean House of Federation of Federal Democratic Republic of Ethiopia.

4/ Any expression in the Masculine gender includes the Feminine.

## PART TWO

## ESTABLISHMENT OF THE CENTER, OBJECTIVE, POWER AND FUNCTION

**3. Establishment**

1/ The Constitution and Federalism Indoctrination Center, (hereinafter called the “Center”) is hereby established as an independent Federal Government Organ having its own legal personality.

2/ The Center shall be accountable to the House of Federation of the Federal Democratic Republic Ethiopia (hereinafter called the “House”).

3/ The Center shall have its head office in Addis Ababa and may open branch offices at Regions and City Administrations as may be necessary.

**፬. <u>ዓላማ</u>**

የማዕከሉ ዓላማ ንቃተ ሕገ-መንግስቱ ያደገና ሁለንተናዊ ተሳትፎ የሚያደርግ ሕገመንግሥታዊ ማህበረሰብ መገንባት ይሆናል፡፡

**፭. <u>የማዕከሉ ሥልጣንና ተግባራት</u>**

ማዕከሉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የሕገመንግስትና ፌደራሊዝም አስተምህሮ ተግባራዊነትን የሚያግዙ የአሠራር ሥርዓቶችን ይዘረጋል፤

፪/ የሕገመንግስትና ፌደራሊዝም አስተምህሮ ስራዎችን ለሚያከናውኑ አካላት የአሰልጣኞች ስልጠና ይሰጣል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤

፫/ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ንቃተ ሕገመንግሥትና ፌደራሊዝምን የሚያጎለብቱ ስልጠናዎችን ይሰጣል፤ የምክክር መድረኮችን ያዘጋጃል፤

፬/ የሕገመንግስትና ፌደራሊዝም አስተምህሮ ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል መርሐ ግብርና ፕሮጀክቶች ይቀርፃል፣ የስልጠና ሞጁል ያዘጋጃል፤

፭/ ንቃተ ሕገመንግሥትና ፌደራሊዝምን የሚያሳድጉ የተለያዩ የህትመት ውጤቶችን በማዘጋጀት ያሰራጫል፤

፮/ በሕገመንግሥትና ፌደራሊዝም አስተምህሮ ዙሪያ የጥናትና ምርምር ስራዎችን ያካሂዳል፣ የተሻሉ ተሞክሮዎችን በመቀመር እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

፯/ አገራዊ የሕገመንግሥትና አስተምህሮ የጋራ መድረክ በማዘጋጀት አፈጻጸምን ይገመግማል፣ የልምድ ልውውጥ ያካሂዳል፣ የወደፊት አቅጣጫ ያመላክታል፤



**4. <u>Objective</u>**

The Objective of the Center shall be to create constitutional society that comprehensively engages in the dynamic of the country by ensuring comprehensive awareness of the constitution.

**5. <u>Powers and Functions of the Center</u>**

The Center shall have the following powers and functions:-

1/ Introduce system that would assist the implementation of the Constitution and Federalism Indoctrination;

2/ Provide training to trainers of the organs and entities that are mandated to provided training on Constitution and Federalism and follow-up their implementation;

3/ Coordinate with the stake holders and provide different trainings on Federalism and Constitution that would enhance the awareness of various parts of the society and arrange consultation forum;

4/ Design programs and project that ensures the effectiveness of the Indoctrination on the Constitution and Federalism, and prepare training modules;

5/ Publish and disseminate various publications that would enhance awareness on Constitution and Federalism;

6/ Conduct research and studies on the area of Constitution and Federalism Indoctrination and formulate and promote best practices;

7/ Organize national forum on the Indoctrination of Constitution and Federalism and conduct assessment of their performance, experience sharing, and indicate future directions;

፰/ አዳዲስና ዘመናዊ የሕገመንግስትና ፌደራሊዝም አስተምህሮ ዘዴዎችን ይቀይሳል፤

፱/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

፲/ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የማዕከሉ አደረጃጀት

**፮. የማዕከሉ አቋም**

ማዕከሉ፡-

፩/ አማካሪ ኮሚቴ (ከዚህ በኋላ “ኮሚቴ”) እየተባለ የሚጠራ፤

፪/ የፌደሬሽን ምክር ቤት አባል ያልሆነና በመስኩ በቂ ሙያዊ ብቃት ያለው ሆኖ በምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ አቅራቢነት በምክር ቤቱ የሚሾም አንድ ዋና ዳይሬክተርና ምክትል ዋና ዳይሬክተር፤

፫/ አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

**፯. የኮሚቴ አባላት**

ኮሚቴው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

፩/ የምክር ቤቱ አፈ ጉባኤ …………………………ሰብሳቢ፤

፪/ የምክር ቤቱ ምክትል አፈ ጉባኤ…………..ምክትል ሰብሳቢ፤

፫/ የምክር ቤቱ የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዎች……..አባላት፤

፬/ የምክር ቤቱ የቋሚ ኮሚቴ ፀሐፊዎች……..አባላት፤

፭/ በዋና ዳይሬክተሩ አቅራቢነት በምክር ቤቱ አፈ ጉባኤ የሚሰየሙ ሦስት የዘርፉ ምሁራን ……………………………………………..…አባላት፤

፮/ የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር……………………ጸሐፊ::

8/ Devise new and updated indoctrination methods on federalism and constitution;

9/ Own property, enter into contract, and sue and be sued on its own name;

10/ Undertake other activities necessary for the attainment of its objectives

## PART THRE

## ORGANIZATION OF THE CENTER

**6. Organization of the Center**

The Center shall have:

1/ An Advisory Committee (here in after called the “Committee”)

2/ One Director General and Deputy Director General recommended by the Speaker of the House and appointed by the House who shall not be member of the House and have the required knowledge in the field;

3/ The necessary staffs.

**7. Members of the Committee**

The Committee shall have the following members:

1/ The Speaker of the House…………..…….Chairperson;

2/ The Deputy Speaker of the House ……………….. ………………………...……...….Vice Chairperson;

3/ Chairpersons of the standing committees of the House……………….………..……..…....members;

4/ Secretaries of the standing committees of the House…………………..……..………….members;

5/ Three professional of the field to be recommended by the Director General and be assigned by the Speaker of the House……...……….……..members;

6/ The Director General of the Center …..….Secretary.

## ፰. የኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት

ኮሚቴው የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩/ ማዕከሉን በፖሊሲ ጉዳዮች እና በሚያዘጋጃቸው መመሪያዎች ላይ ምክረ ሀሳብ ይሰጣል፤

፪/ በማዕከሉ ድርጅታዊ መዋቅር እና የደመወዝ ስኬል ጥናት ላይ ምክረ ሀሳብ ይሰጣል፤

፫/ የማዕከሉን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራም እና በጀት ገምግሞ ያፀድቃል፡፡

፬/ ማዕከሉ በተፈቀደለት በጀት እና ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራም መሰረት ተግባራትን ስለማከናወኑ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

፭/ የማዕከሉን ጠቅላላ የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ገምግሞ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡

## ፱. የኮሚቴው ስብሰባ

፩/ ኮሚቴው በዓመት ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያካሂዳል፡፡ ሆኖም እንደአስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባዎችን ሊያካሂድ ይችላል፡፡

፪/ ከግማሽ በላይ የሚሆኑ የኮሚቴ አባላት በስብሰባው ውስጥ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

፫/ የኮሚቴው ምክረ ሀሳብ በድምጽ ብልጫ ያልፋል፤ ድምጽ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ያልፋል፤

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ኮሚቴው የራሱን የስብሰባ ሥርዓት የውስጥ አሠራር ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፲. የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባራት

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የማዕከሉ ዋና ስራ አስፈፃሚ በመሆን የማዕከሉን ሥራዎች ያደራጃል፣ ይመራል፣ ያስተዳድራል።

## 8. Function and Duty of the Committee

The Committee shall have the following function and duties:

1/ Provide advice to the Center on policy matters and Directives prepared;

2/ Provide advice on studies related to structure and salary scale of the Center ;

3/ Review and approve annual work programs and budget of the Center;

4/ Follow up and support the Center to comply with annual work program and approved budget;

5/ Review and give direction on performance report of the Center.

## 9. Meeting of the Committee

1/ The Committee shall hold bi-annual regular meetings. However it may conduct extra ordinary meetings as may be necessary.

2/ There shall be quorum when half of the members of the Committee are present at a meeting.

3/ The Committee shall pass its advice with majority vote; in case of ties the Chairperson shall have casting vote.

4/ Without prejudice to the provision of this Article the Committee may adopt its own meeting rules.

## 10. Power and Functions of the Director General

1/ The Director General shall be the chief executive officer of the Center and shall organize, manage and administer operation of the Center.

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፭ የተመለከቱ የማዕከሉን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የማዕከሉን ሠራተኞች የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግን አጠቃላይ መርሆችን መሰረት በማድረግ ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የማዕከሉን የአስተዳደር መመሪያዎች ሲፀድቁ ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ) የማዕከሉን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራም እና በጀት አዘጋጅቶ ለኮሚቴው ያቀርባል፤ በመንግሥት ሲጸድቅም በስራ ላይ ያውላል፤

ሠ) ለማዕከሉ በተፈቀደለት በጀት እና ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራም መሰረት የፋይናስ ሕግን ተከትሎ ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ረ) የማዕከሉን ጠቅላላ የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ያዘጋጃል፣ በኮሚቴው ተገምግሞ ከጸደቀ በኋላ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፤

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለማዕከሉ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለማዕከሉ ምክትል ዋና ዳይሬክተር እና ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች ወይም ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

## ፲፩. የምክትል ዋና ዳሬክተር ሥልጣንና ተግባር

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ተጠሪነቱ ለማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፤

2/ without prejudice to the generality of sub-article (1) of this Article, the Director General shall:

a) Exercise the power and functions of the Center stipulated under Article 5 of this Proclamation;

b) Employ and administer Employees of the Center in accordance with basic principles of the Federal Civil Service Laws;

c) Implement Directives of the Center up on approval;

d) Prepare and submit annual work program and budget of the Center to the Committee and implement same up on approval by the Government;

e) Effect expenditure based on the annual work program and approved budget of the Center in compliance with financial law;

f) Prepare performance report of the Center and up on review and approval by the Committee, submit same to the House.

3/ The Director General may delegate part of his powers and function to the Deputy Director General or to the other officials and employees of the Center for efficient and effective performance of the activities of the Center.

## 11. Power and Function of the Deputy Director General

The Deputy Director General shall be accountable to the Director General of the Center and shall have the following powers and functions:

1/ Act on behalf of the Director General in his absence;

፪/ ከዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፤

## ፲፪. በጀት

የማዕከሉ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች ይሆናል፡-

፩/ ከመንግስት የሚመደብ በጀት፤

፪/ ከስጦታ እና ከእርዳታ፤

፫/ ከማንኛውም ሌላ ህጋዊ ምንጭ ይሆናል፡፡

## ፲፫. የሒሳብ መዛግብት

፩/ ማዕከሉ የተሟላና እና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡

፪/ የማዕከሉ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በፌደራል ዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል፡፡

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## ፲፬. ባለድርሻ አካላት

ባለድርሻ አካላት በሚያከናውኗቸው ስራዎች ውስጥ የሕገመንግሥትና ፌደራሊዝም የአስተምህሮ ተግባራትን የማካተት፣ ለአመራሮችና ሰራተኞች የሕገመንግሥትና ፌደራሊዝም ግንዛቤያቸውን የማሳደግ፣ የተለያዩ የአሰራር ሥርዓቶችን በመዘርጋት የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማጎልበት ከማዕከሉ ጋር ተባብሮ የመስራት ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## ፲፭. የጋራ መድረክ

፩/ ማዕከሉ በሕገመንግሥት አስተምህሮ ዙሪያ ከልህቀት ማእከላት እና ከባለድርሻ አካላት ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ የጋራ መድረክ በማዘጋጀት አፈጻጸሙን ይገመግማል፤ የልምድ ልውውጥ ያካሂዳል፤ የወደፊት አቅጣጫ ያመላክታል።

2/ Perform other activities specifically referred to him by the Director General.

## 12. Budget

The Budget of the Center shall be from the following sources:

1/ The Budget allocated by the Government;

2/ From gifts and donations ;

3/ from any other legal sources.

## 13. Books of Accounts

1/ The Center shall keep accurate and complete books of account.

2/ The books of accounts and financial documents of the Center shall be audited annually by the Federal Auditor General or Auditor assigned by him.

## PART FOUR
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

## 14. Stakeholders

Stakeholders shall incorporate in their activities Constitution and Federalism trainings enhance the management and employees on Constitution and Federalism awareness, introduce systems to this effect, and develop the awareness and understanding of the public by working together with the Center.

## 15. Plenum

1/ The Center shall organize joint plenum with Center of Excellences and Stakeholders at least twice a year in order to assess performance, exchange experience and set out future directions.

፪/ ማዕከሉ የልህቀት ማዕከላትና የባለድርሻ አካላትን የሕገመንግስትና ፌደራሊዝም አስተምህሮ አፈፃፀም ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ ግብረ መልስ ይሰጣል፡፡

### ፲፮. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

የፌደሬሽን ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

### ፲፯. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሚያዚያ ፩ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

2/ The Center shall support and monitor the performance of the Center of Excellences and Stakeholders with regards to Constitution and Federalism teachings and provide feedback.

### 16. Power to Issue Directive

The House of Federation may issue Directive necessary for the implementation of this Proclamation.

### 17. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazetee

**Done at Addis Ababa, 9th Day Of April 2019,**

**SAHLEWORK ZEWEDIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**